# ሆድ፣ ድርጅትና ውድ ሀገር

እነሆ ይሄም ተነግሮ ነበር

ከሦሥት ዓመት በፊት በፍኖተ ራዲዮ ተነበ የነበር ሐተታ

የመጀመሪያው ከሁለቱ ይጣላል ። ሆዳም ሰው አይደራጅም ፤ መደራጀትም አይፈልግም፤ በድርጅት ከገባም ሳይውል ሳያድር ቃል ኪዳኑን አጥፎና ክዶ ድርጅትን ያፈርሳል፤ ይበትናል፤ ለጠላት ያጋልጣል ። በታሪክና በራሳችንም ተመክሮ ያየነው ነው ። ሆድ ከቀደመ ሀገርም ለጥቃት ትጋለጣለች። የዘንድሮ ሰው ምነዋ አንበጣን መሰለ ያሉት እናት ችግሩን ግልጥልጥ አደርገዋል ። ሆድ ሲቀድም ሀቅን መካድ መሸጥ፤ ወገንን መካድ፤ ባንዳ አንጃ መሆን ይሰፍናል ። ሆዳሞችም ትላንት ቆምንለት ያሉትን መርህ፤ ድርጅታችን ነው ያሉትን፤ ጓዴ ሀገሬ ያሉትን ሁሉ አሽቀንጥረው ጥለው ከርሳቸውን ለማስታገስ ወዲህ ወዲያ ሲሉ፤ እንደ ፖለቲካ ፌንጣ ሲዘሉና ሆዳም ጉማሬ ሆነው ሲጨቀዩና ሲዋረዱም ያየነውና እያየነው ያለ ነው ። ሆድና ሀገር ተጻራሪ ናቸው። ወይኔ ለሆዳሞች!

ድርጅትና ሀገር አብረው ተጓዥ ናቸው ። ሀገርን ከውድቀትና ጥፋት ለማዳን መደራጀትን ይጠይቃል ። ያልተደራጀ ሕዝብ የተበታተነ ጭራሮ ነው --ችቦ መሆን አይችልም ። በደማቁ አያበራም ። የድርጅት ይዘትና ሚና ግን ተደራጀን ለሚሉትም ምስጢር ሆኖባቸዋል ። አባላትና ዜጎች ለድርጅታቸው ታማኝ ሲሆኑ ትርጉሙ ይጠፉቸዋል ። ድርጅትን ከሀገር በላይ ይወዳሉ ብለው ሊነቅፉም ይዳዳቸዋል ። የሀገር ወዳድ ድርጅት አባላት ድርጅታቸውን የሚያፈቅሩት ለሀገር በመቆሙ መሆኑን ይስታሉ ። ለትግልና ሀገርን ለማዳን ድርጅት አያሻንም ብለው ሊሰብኩ የጣሩ መጤ ፖለቲከኞችና አወናባጆችም ጥቂቶች አልነበሩም ። ጸረ ድርጅት ጪሂዎች አሉታዊ ሚናቸው ከቶም የሚናቅ አይደለም ። ለ 21 አመት አሽመድምደው ይዘውን አሉ ። ከድርጅት ወደ ድርጅት፤ ከአቅዋም ወደ አቅዋም እየዘለሉ በዚህ በዚያ እየተጣዱ ግና በዋናው መልክ የወያኔ ጠላት የሆኑትን ድርጅቶች ለመናድ  ሲጥሩ መታዘብ ተገደናል ።ሆድ እኮ ክፉ ነው ሰውን የሚያዋርድ ሀገር የሚያጠፋ ሰው እንስሳ እኮ ነው ለከርሱ ሲገዛ የተባለውን ያስታውሷል ።

ድርጅት ማለት በደፈናው ሁሉን አይነት መሰባሰብ ያጠቃልላል ። የፖለቲካ ድርጅት ስንል ግን ለፖለቲካ አላማ የተደራጁትን ይመለከታል ። ዕቁብ ፤ እድር ወይም የሲቪክ ማህበር ማለት አይደለም ። የፖለቲካ ድርጅት ፖለቲካዊ መርሐ ግብር አለው፤ አደረጃጀቱም የራሱ ነው  ከይዘቱና አላማው በመነሳት ። ለፖለቲካ ትግል ፖለቲካ ድርጅት የግድ ያስፈልጋል ። አያስፈልግም የሚሉት አወቁም አላወቁ ሕዝብን ትጥቅ አስፈቺና አደገኛ ናቸው ። ሁሉም ራሱን የፖለቲካ ድርጅት ያለ በርግጥ ነውም ማለት አይደለም ። ድርጅት ለመባል መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች አሉ ። መጀመሪያ ድርጅት ስንል የተደራጁና በአንድ ዓላማ ዙሪያ ሊታገሉ የተዘጋጁ  ግለሰቦች መኖር አለባቸው--በህገ ደንብና የጋራ ስርአት የተሳሳሩ ። ሱቅ በደረቴ በሚባል የሚላገጥባቸው የአንድ ግለሰብ ድርጅቶች (አባሉም መሪውም አንድ ወይ ሁለት ግለሰቦች የሆኑባቸው) ፤ራሳቸውን ግንባር ወዘተ ቢሉም ቁጠር ንብዝ ሲባል ያውም ተባበርን ብለው ደርዘን መሆን የሚያቅታቸው ፤ የወያኔ መሳለቂያ ያልሆኑ ማለትም ነው ። በአንድ ትንሽ አፍሪካ ሀገር ከ 170 ያላነሱ "ድርጅቶች" አሉ

። በሀገራችንም  ድርጅት ነን ባዮች ዕድሜ ለወያኔ ፈልተዋል-- ተለጣፊዎችም ጥቂት አይደሉም ። ስንቶቹ ናችው የራሳቸው ነጻ የፖለቲካ አቅዋም ያላቸው? ስንቶቹ ናቸው በተጨባጭ የሚታገሉት? በባዕድ ሀገር ካሉትስ እውን ይህ ነው የሚባል  አባልና እንቅስቃሴ ያላቸው ስንት ናቸው?

ፖለቲካ ዛሬ ከቧልት አልፎ ንግድ ሆኗል ። አፍሪካን አሜሪካኖች ገንዘብ ለፖለቲካም ሲፈልጉ ቤተክርስቲያን ይመሰርቱ ነበር ። ዛሬ በእኛም ዘንድ ፖለቲካ ለገንዘብ መሆኑ በግልጽ እየታየ ነው ። ዜጎች አዋጡ እየተባሉ ይጨቀጨቃሉ፤ ይደለላሉ፤ማስፈራሪያ ጫናም ይመጣባቸዋል ። የፈሩና የጨነቃቸው ብቻ ሳይሆኑ ሌሎቹም ነገር አለሙ ያልገባቸውም ዛሬም ቢሆን ያዋጣሉ ። በ ጠራራ ጸሐይ ይዘረፋሉ ። የሚያሳዝነው ግን መታለልና መዘረፍን የመረጠ ትውልድ የመጣ ይመስል ሲዘረፍ የሚነቃ ዜጋ ጠፍቶ ዛሬም ፖለቲካን ለዝርፊያ የሚጠቀሙ ነጋዴዎችና አጭበርባሪዎች እየተጫወቱበት ነው ። በድርጅት ስም ጸረ ድርጅቶች በዝተዋል ። ወያኔም የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዳይደራጅ ይፈልጋልና (መፈለግም አለበትና) በተቃዋሚ ድርጅት ሽፋን አፍራሾቹን አሰማርቷል ። የወያኔ ትኩረት ጠላቴ በሚላቸው ድርጅቶች ላይ ነውና እነዚህን ለመበተን ለማፍረስ የሚዳከሩትን ማወቁ ማን ለወያኔ እየሰራ መሆኑን ይጠቁማል ።

ድርጅት የፖለቲካ ዓላማ፤ ግብ፤ መርሀ ግብር ያስፈልገዋል ። ይህን የሚጻረሩ አሁንም የህዝብን ትግል ወደዱም ጠሉም የሚጎዱ ናቸው ። ግቡ ምን ምን መሆኑንና ይህን ግብ እውን ለማድረግም ምን ማድረግ እንዳለበት በግልጽ ማስፈር ማስቀመጥ ይኖርበታል ። ጠላትን ወዳጅ ወዳጅን ጠላት የሚልበት ሁኔታ ከተከሰተ ወይም የትግሉን ይዘት መረዳት ከተሳነውና ሊንቀሳቀስ የተነሳው የሕዝብን ፍላጎት ለማሟላት ሳይሆን ለግለሰቦች ስልጣን ጥም ማርኪያ ከሆነ ገና ከጠዋቱ ተሽመድምዶ ይቀራል ። የታዘብነው ነው ።  የሕዝብ ድርጅት በሉኝ የሚል ከሆነማ የሚጠበቅበት ብዙ ነው ። ዛሬ ግርግር ለሌባ ያመቻል እንዲሉ በዚህም በዚያም የድርጅት መሪዎች ነን ባዮች፤ ስድስት ወር ብቻ ስጡንና ነጻ ልናወጣችሁ ነው ብለው በድፍረት ሳያፍሩ የሚነግሩን ዓይን አውጣዎች በርክተዋል ። ፖለቲካ እንደማንኛውም ስምሪት እውቀትን ይጠይቃል። ያኔ ያኔ ማንም ድርጅት በሌለበት ድርጅት መስርተው ሊታገሉ የሞከሩትና የተሳካላቸውም ቢሆኑ ቀደም ሲል ንቃታቸውን ለማዳበር በማይናቅ ደረጃ ጥረዋል ። ዛሬ ግን ከብዙ ተመክሮ በኋላ መንቃት ማወቅ፤ ከድርጅትና አደረጃጀት ተመክሮ መማር ሐጢያት የሆነ  ይመስል ድርጅት ነን የሚሉን መደናበርና የባጥ የቆጡን መቀባጠር ቀንቷቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ መሳቂያ መሳለቂያ አድርገውናል ። ያለፉ ስህተቶችንም ዘው ብለው ገብተው ይደግሟቸዋል ። ሀ ሳይሉ ፍ ፍርሻ ይመጣባቸዋል ። ያሳዝናል ብንል አይበዛም ።

ደግሞ ደጋግሞ የሕዝብ ጎራ ተብየውን መውቀሱ ተገቢ ነው ። በሽታውን የደበቀ መድሐኒት አይገኝለትም ተብሏል ። አስመሳዩን ማጋለጥ ደግሞ ግዳጅ ነው ። ሀገርን የሚመለከት ጉዳይ በሽፍንፍንና በተወው እባክህ የሚዘጋ አይደለም ። ለዚህም ነው ራሱ የሕዝብ ጎራ ወይም ታጋይ ድርጅት ነኝ የሚለውን ሁሉ በኩራዝ ሳይሆን በቅርበት ባውዛ መመርመሩ አስፈላጊ የሚሆነው ።  ድርጅቱ ግን በሀቅና ከልብ ለሀገርና ሕዝብ ቆሞ  ግንዛቤና ሞያተኛነት የጎደለው ከሆነ ሂስ ለማጋለጥና ለመጉዳት ሳይሆን ለማረምና ለማረቅ መሆን ይገባዋል ። በሀገር ጉዳይ ግን አትንኩኝ አትንኩት የሚባል የሹም ዶሮ የለም ። ሁሉም ይገመገማል፤ ሁሉም መወቀስ ካለበት ይወቀሳል ። ጣዖት ጠረባው ይቁም የተባለው አለምክንያት አልነበረም ። ገና ምግባሩና ጽናቱ/ጽናቷ ሳይፈተን ተክለ ስብ ሙገሳው  እየተጧጧፈ ግለሰቦች ወደ ግብዝነት

ተገፋፍተው በዚያው ወደ ውድቀታቸው ያመራሉ-- የሕዝብ የተባሉት የባዕድም የወያኔም ሆነው ይጋለጣሉ ። ይህንንም ነጋ ጠባ ያያነው ነው ። ከዚህ ጋር ተያይዞ ደግሞ የድርጅቶች ታማኝነትና በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነትን በተመለከተ መሠረታዊ ጥያቄ መነሳቱ አይቀሬ ነው ። ለመሆኑ ድርጅቶች ለራሳቸው ከሚሰጡት ግምትና ቦታ፤ ስያሜና ድጋፍ ውጪ ሕዝብ ምን ይላል ? ያምናቸዋል ወይስ ይንቃቸዋል ? የእኛ ይላቸዋል ወይስ የወያኔ ወዳጆችና የባዕድ ቅጥረኞች ? ይከተላቸዋል ወይስ ጀርባውን ይሰጣቸዋል? ማንኛው ድርጅት ነው በሕዝብ የሚታመን? በሕዝብ ውስጥ የፖለቲካና የድርጅት ሥራን እየሰራ ያለው? ለመሆኑ ድርጅቱስ እነማንን አቅፏል? ሊዘነጉ ወይም ሊረሱ የማይችሉ ጥያቄዎች ናቸው ።

ድርጅት ወይም ታዋቂ አባሎቹና መሪዎቹ የቆሸሸና ጸረ ሕዝብ ሊያሰኝ የሚችል ታሪክ ሊኖራቸው አይገባም ። በዚህ ብቻ የተነሳ ሕዝብ መቼም አመኔታን አይሰጣቸውም ። በደልና ቂም አለና ። በዳይ ይቅር በሉኝ ካላለ ደግሞ ቂም ሊጠፋ አይጠበቅም-ቢያንስ አስቸጋሪ ይሆናል ። በመሆኑም ዛሬ በብዙ ተቃዋሚ ነን ባይ ድርጅቶች የቀይ ሽብር ወንጀለኞች መኖራቸው ሕዝባዊ ድጋፍን ጠሪ አይደለም ። ኢትዮጵያን እንወዳለን ካሉም ከፖለቲካው መድረክ መራቃቸውና ዝምታቸው--ይቅርታ መጠየቅን እስከፈሩ ድረስ-- የሚፈለግ ነው ። ከአጼውም፤ ከደርግም ከወያኔም ጋር ተቃቅፈው የከረሙም በተለይ ዝምታን፤ ንስሐ ጥየቃን ቢመርጡ ነው የሚሻለው የፖለቲካውን መድረክ ከመረበሻቸው ይልቅ ። የወያኔ ዋና ባልስልጣን ሆነው ስንቱን ንጹህ ኢትዮጵያዊ ከፈጁ ካስፈጁና ሀገርንም ካስገነጠሉና ከጎዱ በኋላ ዛሬ እኛ ነን ታጋይ ለኢትዮጵያ የሚሉትንም ላጠፋችሁት ሁሉ በቅድሚያ አጠፋን ብላችሁ ከሕዝብ ይቅርታንም ምሕረትንም ጠይቁ ማለቱ ሲያንስ ነው ። ስማቸውን ባንጠቅስም እነዚህ ሁሉ ዛሬ ምን ቢለፈልፉ የትላንት ወያኔዎችን ሕዝብ ሊያምን አይጠበቅም--በማያከራክርና በማያወላዳ መንገድ አጠፋን ማሩን እስካላሉ ድረስ ። እነዚህን ደግሞ ጀግና ሀገር ወዳድ የሚሉ የኢትዮጵያ ወዳጆች ሊባሉ አይችሉም --ማፈሪያ እንጂ ። የፈሰሰው ደምና የደረሰው ግፍ ጨዋታ አይደለምና ። በቀይ ሽብርም ወርቅ ትውልድ ተፈጅቷልና ነፍስ ገዳዮች ወይም ክለየላቸው አረመኔዎች ጎን ሆነው የሰሩና ወንጀል የፈጸሙ ከዛሬው ትግልና ፖለቲካ መወገድ አለባቸው--በተለይም የገማ የገለማ ደርጋዊና አረመኔ አቅዋማቸውን አሁንም ሊቀጥሉ ሲቃጡ ።

ይህ አሳዛኝ መደናገር ( ወይም ለማደናገር ጥረት) ወያኔ ትኩረት ሰጥቶ እያራገበው ነው ። ገንዘብ አፍሶ ሰርጎ ገቦችና አስመሳይ ሀገር ወዳዶችን አሰልፏል ። በነዚህ አማካይነትም ድርጅቶችን ከፋፍሏል፤ በአንጃ ጎድቷል ። በዚህ ርኩስ ተልዕኮው ኣሜሪካ፤ እንግሊዝ፤ ወዘተ ሙሉ ትብብርን በማድረግ በውጭ ሀገር ነዋሪው ኢትዮጵያዊ ላይ ስለላን እንዳጧጧፉ አሉ ። ዜጎች ደግሞ ሙያተኛ የድርጅት ስራን የዘነጉ ወይም የማያውቁ ሆነው ይገኛሉና ምስጢር መሆን የሚገባው በየድረገጹና የውይይት መድረኩ ሲረጭ እየታየ ነው ። ይህ ደግሞ ለወያኔ ሲሳይ ሆኖ ቆይቷል። ለዚህም ነው ስለ ድርጅት ይዘት፤ አላማ አስራርና አደረጃጀት በቂ ግንዛቤን መያዝ የግድ ሆኖ የሚገኘው ። መደዴ መሪዎችና ቀሽም ድርጅቶች ዜጎችን ገና ከጠዋቱ ለጥቃት የሚያጋልጡ ናቸው ። ለዚህ ሁሉ ደግሞ በርካታ ምሳሌዎች እንዳሉ በርካታ ዜጋ የሚያውቀው የምታውቀው ነው። አድርባዮችና ለሆዳቸው የተገዙ ደግሞ ቀና አሳቢ ድርጅትን ከውስጥ ቦርቡረው ለውድቀት ያደርሱታል ። የንዋይ ፍቅራቸው፤ የስልጣን ጥማቸው፤ ወኔ ቢስነታቸው ቅጥረኛም አላዋቂም የወያኔ ቡችላ ያደርጋቸዋል ። ጉዳቱ ቀላል አልነበረም፡ አይደለምም። ዜጎች ለወያኔ ተንኮል (ያውም ለተነቃና ለታወቀ) ሰለባ ሆነው ራሳቸውን ለጥቃት ሲያጋልጡ በተደጋጋሚ አይተናል ። ለምሳሌ የአገዛዙን ሰላይ ደብድቦ ወይም የተጎዳ አስመስሎ

ተቃዋሚዎች ከታሰሩብት ማጎሪያ መከተትና የስላላ ስራውን ማሳካት ድሮም ጀምሮ የሚታወቅ ነው። ይህ ግን ከዕውቀት ወይም ከግንዛቤ ጋር በመጣላቱ ዛሬም ለዚህ ዘዴ ድርጅቶች (ዜጎችም) ሰለባ እየሆኑ ሰላዩን ቅጥረኛውን ታጋያችን መሪያችን ብለው ሲያወድሱም ታዝበናል ።

ከዚህ ተያይዞ የተከሰተ ትልቅና ጎጂ ስህተት ሀቀኛ ሀገር ወዳዶችን፤ ሕይወት የገበሩ ጀግኖችን ሁሉን ወይም በአብዛኛው ማከችልችልና ለሀገር መሰዋትን ከሞኘነት ወይም ካልሰለጠነ ፖለቲካ ጋር ማዛመድ ነው ። ይህ በአብላጫው ከፖለቲካ መሐይምነትና ከፍርሃት (ወይም ቅጥረኛነት) የመነጨ ጎጂ አቅዋም ሀገር አድኑን ትግል በአያሌው ጎድቷል ። ለሀገር የተሰዉትን፤ ስየል የተቀብሉትን፤ ሲታገሉ ይህ ነው የማይባል ጉዳት የደረሰባቸውን በመዘከርና በማመስገን ፈንታ ነጋ ጠባ የስድብ ውርጅብኝ እያወረደባቸው ያን የሰማ ዜጋ ወደ ትግል የሚገባበት በር አጠገብም መታየት እንደማይፈልግ ግልጽ ነው ። ወጣቱን ትውልድ ወያኔ በአልባሌ ልምዶችና በዘቀጡ ባህሎች እያሽመደመደ ባለበት በታገሉና በአቅዋማቸው ጸንተው ዛሬም ወያኔን እየታገሉ ባሉት ላይ የሚደረገው የማጥላላት ዘመቻ አርበኞች አርአያ እንዳይሆኑ ያደርጋል ። ሶማሌዎች ኩጂሪ ካብህ እንዲሉ የቻልክ ሁሉ ነፍስ አውጪኝ በል፤ ራስክን ጠብቅ፤ አትጋፈጥ ማለትና ፍርሐት ይሰፍናል ። ሀገር አድኑ ትግል ደግሞ ተወደደም ተጠላም መስዋዕትነትን ይጠይቃል ። አለ መስዋዕትነት ሀገር ስርየት ታገኛለች፤ አረመኔውና ሰው በላው የወያኔ አገዛዝ ይወድቃል ብሎ ማስብ ቀርቶ ማለሙ ፋራነት ብቻ ሳይሆን የፈሪዎች ነው ። ፈሪ ደግሞ ሀገሩን አያድንም ።

ለመሆኑስ እናድናት የምንላት ሀገር ማናት ? በዚህም ላይ ዛሬም ውዝግብ መኖሩ ምንኛ ዘረኛው ወያኔ እንደከፋፈለንና በጥላቻና ይመጣል ተብሎ በሚቋመጥ ጥቅም እንደተጫወተብን ያረጋግጣል ። አንቀጽ 39 ለማንም ሳይሆን ለወያኔ/ትግራይ ዋስትና የተዘጋጀ ሆኖ ሳለ ለእኛ ይጠቅማል ብለው ያኔም በፈረደበት አማራ ላይ አጓርተው የወያኔ መጫወቻ የሆኑ ነበሩ ። ለውርደትና ስደት ተዳርገው ስንት ዓመት ካለፋቸው በኋላም ዛሬም ፈደራል መዋቅሩን እናጠናክር፤ አንቀጽ 39ን እንወዳለን እያሉ ወያኔን በመማጠንና ከስደት ጥራን አቦ በማለት ራሳቸውንም ለባሰ ውርደት በማጋለጥ ላይ ናቸው ። ኢትዮጵያዊነታቸውን የሚክዱና አሁንም እንደራደር በዚህ ጉዳይ የሚሉ አሉ ። ትግላችን ጸረ አማራ ነው ብሎ፤ ሸዋ ተራማጅ ልጆቹ ሳይቀሩ ትምክህተኞች ናቸው ብሎ ትግል የጀመረው ወያኔ 21 ዓመት ሙሉ ጸረ አማራነቱን፤ ጸረ ኢትዮጵያነቱን ሲያሳይ ከርሞ እያለ ዛሬ አማራዎችን ከዚህ በዚያም ሲያባርርና ሲመነጥር አዲስ የሚሆንባቸውም አሉ ። የመጣባቸው፤ በሀገር ላይ የመጣው መዓት መርገም ይዘቱና ክፋቱ ከቶም ያልገባቸው ። ሀገር አድን ትግል ይህን ዓይነት መሞኘት/መዘናጋት አይፈቅድም ። አማራው ሕዝብ ተፈናቀለ ሲባልም በተቃውሞ ሰልፍ (ባዕድ ሀገር) የሚሳተፉት ቁጥር አሳዛኝና ጥቂት ነው ። የምንታገለው ለክልል፤ ለጎሳና ጎጥ፤ ለብሔረስብም ሳይሆን ለውድ ሀገር ኢትዮጵያ ነው ። ይህን አሌ የሚለው ወያኔ ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚ ድርጅት ነን የሚሉም ጭምር ናቸው ። አገር አድን ትግሉ ብዙ እንቅፋቶችና ጋሬጣዎች ተደቅነውበታል ።

--ሀገራችን ኢትዮጵያ አይደለችም የሚሉ

==ወያኔ ጠላታችን አይደለም የሚሉ

--ሆዳቸውን አስቀድመው ሀገርንም ድርጅቶችንም የሚጎዱ

-- ለወያኔ የሚጠቅም ትጥቅ አስፈቺ ቅስቀሳ የሚያደርጉ

-- ሀገር ወዳድ ድርጅቶችን የሚከፋፍሉ

--- ወያኔን መፋለም ሲገባ ማመጽ ሐጢያት ነው የሚሉ

== ጀግኖችን የሚያክቸለችሉ

ወዘተ ሁሉም ሀገር አድኑን ትግል ሲጎዱ ቆይተዋል፤ እየቀጠሉም ናቸው ።

ይህን ሁሉ መገንዘብ፤ ማጤንና እርምት ማድረግ ቀነ ቀጠሮ የማይሰጥ የሀቀኛ ሀገር ወዳዶች ግዳጅ ነው ። ይህ ትችትም

ይህን ለማሳሰብ የታቀደ ነው ።